# የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ስጋት ሥራ አመራር የአሰራር ማንዋል

ሃምሌ 2007

አዲስ አበባ

3-0/273/07

29 ሐምሌ 2007

ኢትዮጵያ ... ሪፐብሊክ
የኢትዮ... 
The Fe... ...blic
Ethiopian Revenue... Customs Authority

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

<u>በያሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>ማኑዋል መለክን ይመለከታል</u>

የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት አሰራሮችን ወጥ በማድረግ ተጠያቂነት እና ኃላፊነት በግልጽ የሚያሳይ አሰራር ለመዘርጋት ጥረቶችን እያደረግ ይገኛል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ፡-

1. የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ስጋት ስራ አመራር የአሰራር ማኑዋል
2. የካርጎ ስካኒንግ ስጋት ስራ አመራር ማኑዋል

ለስጋት ስራ አመራር ኮሚቴ ቀርበው ከታዩ በኋላ ማስተካከያ እንዲደረግባቸው ተደርጓል፡፡ በዚሁ መሠረት ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ ተደርጎ በተያያዘላቹ የአሰራር ስርዓት መሠረት ስራዎችን በወጥነት እንድታከናውኑ እየገለጽኩ በማኑዋሉ መሠረት ስራዎችን በምታከናውኑበት ወቅት የሚያጋጠሙ ችግሮች ካሉ ለታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት እንድታሳውቁ አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሳሙኤል ገዛኸኝ
ምክትል ዳይሬክተር
የጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ

<u>ግልባጭ</u>

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለህግ ማስከበር ሥራዎች ዘርፍ
- ለታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት

<u>ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን</u>

**ቅንጫፍ ጽ/ቤቶች**

- ➢ አ/አ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
- ➢ አዲስ አበባ ኤርፖርት ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

**አዲስ አበባ**

- ➢ ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **አዳማ።**
- ➢ ለድሬደዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ድሬደዋ።**
- ➢ ለሐዋሳ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ሐዋሳ።**
- ➢ ለባሕርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ባህር ዳር።**
- ➢ ለመቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **መቀሌ።**
- ➢ ለኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ኮምቦልቻ።**
- ➢ ለሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ሞያሌ።**
- ➢ ለሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ሚሌ።**
- ➢ ለጂጂጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ጅጂጋ።**
- ➢ ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ሞጆ።**
- ➢ ለጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  **ጋላፊ።**

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

## የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ሥራ አመራር ዳይሬክቶሬት

### የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች ስጋት ሥራ አመራር የአሠራር ማኑዋል

ሐምሌ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ምዕራፍ አንድ

1.1. መግቢያ...1

1.2. የተቋሙ ራዕይና ተልእኮ መግለጫ...3

1.3. ዓላማ...4

1.4. አስፈላጊነት...4

1.5. የተፈጻሚነት ወሰን...4

1.6. ትርጉም...5

ምዕራፍ ሁለት፡-የስጋት ስራ አመራር የአሰራር ፍሰት

2.1. የተግባርት ቅደም ተከተል(ደረጃዎች)...7

2.1.1. የመጀመርያ ደረጃ፡-ስጋቶችን መለየት...7

2.1.2. ሁለተኛ ደረጃ መረጃ፡- ማሰባሰብ እና ማደረጀት...8

2.1.3. ሶስተኛ ደረጃ፡- ስጋት መተንተን እና የስጋት ደረጃ ማውጣት...9

2.1.4. አራተኛ ደረጃ፡- ስጋት መጣልና በሲስተም የተጣለ ስጋት ማሻሻል...11

2.1.4.1.የገቢ ዕቃ ስጋት አጣጣል...11

2.1.4.1.1. በሲስተም ስጋት መጣል በማይቻልበት ሁኔታ...11

2.1.4.1.2. በሲስተም የተጣለ ስጋት በማኑዋል (manually) ማሻሻል...12

2.1.5. የገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ስጋት ደረጃ አጣጣል...17

2.1.5.1. የገቢ ትራንዚት...17

2.1.5.2. የወጪ ትራነዚት...19

2.1.6. የገቢ መንገደኞች የስጋት ደረጃ አወሳሰን...20

2.1.7. ጉምሩክ መጋዘን ድልድል...22

2.1.8.የወጪ ዕቃዎች ስጋት አመዳደብ...24

2.1.9. ደረጃ አምስት፡- የስጋት ደረጃችን ውጤት መከታተልና መገምገም...26

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1. መግቢያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደርን ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል። ከዚህም አንዱና ዋነኛው የጉምሩክ አሠራርን ሙሉ በሙሉ የስጋት ሥራ አመራርን መሠረት ያደረገ ሆኖ የተቀላጠፈ አገልግሎትና ቁጥጥር የተጣጣመ እንዲሆን ማስቻል ነው። የስጋት ሥራ አመራር አለም አቀፋዊ ይዘት ያለው የአሠራር ሥርዓት ሲሆን ለህጋዊ ነጋዴዎች የተቀላጠፈ አገልግነሎት መስጠት፤ ለህጉ ተገዢ ባልሆኑት ላይ ደግሞ ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ እና ወደ ህግ ተገዥነት ለማምጣት የሚያስችል ዘመናዊ የአሰራር ዘዴ ነው። መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች በመሰብሰብና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በመተንተን ፈጣን አገልግሎት አሰጣጥን ከውጤታማ ቁጥጥር ጋር አጣጥሞ ለመተግበር የሚያስችል ስልት ነው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ ባለስልጣኑ ገቢን በብቃት ለመሰብሰብ፣ ኮንትሮባንድን ለመከላከል እና የህብረተሰቡን ደህንነት ለመጠበቅ በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የሚደረገውን ቁጥጥር ስጋትን መሰረት ባደረገ አኳሆን እንዲፈጸም እየሰራ ይገኛል። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ወጥነት ያለው የአሰራር ማኑዋል በአገር አቀፍ ደረጃ ባለመኖሩ ተጠያቂነት እና ወጥነት ያለው አሰራር ተግባራዊ ማድረግ አልተቻለም። እነዚህ ስራዎች በተገቢው ሁኔታ ማከናወን ይቻል ዘንድ ወጥነት ያለው የስጋት ሥራ አመራር ማኑዋል መቅረጽና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው። በስጋት ሥራ አመራር ያልተደገፈ አገልግሎት አሰጣጥ ንግድን የማሳለጥ ተግባር ከማስተጓጎሉ ባለፈ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ ስጋቶችን ለይቶ ትኩረት ማድረግ ሲገባው በሁሉም ላይ ቁጥጥር በማድረግ አላስፈላጊ የሆነ መስተጓጎል እንዲሁም የሃብት ብክነት ያስከትላል።

የጉምሩክ ቁጥጥር የስጋት ሥራ አመራርን መሰረት ባደረገ መልኩ ተግባራዊ ማድረግ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ሲኖሩት በዋናነት ንግድና ኢንቨስትሜንትን ለመደገፍ፤ህጋዊ ነጋዴዎችን ለማበረታታት እና ህገ-ወጥ የንግድ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠርና ወደ ህጋዊ ስርዓት ለማምጣት ከፍተኛ ሚና አለው። ስለሆነም ይህ የአሰራር ማኑዋል ከዚህ በፊት ሲሰራ የነበረ ወጥነት የጎደለው አሰራር ለማስቀረት እና ግልጽነትና ተጠያቂነት በሚያሰፍን መልኩ ስራዎችን ለማከናወን ያለመ ነው።

ማኑዋሉ ሲዘጋጅ በሀገሪቱ የሚገኙ ሁሉም የጉምሩክ ኬላዎችና መቅረጫ ጣቢያዎች ላይ የሚደረጉ የቁጥጥር ሥራዎች በአውቶሜሽን ሲስተም የታገዘ እንደሚሆን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ አሁን ያለው የሲስተም የጥራት ክፍተትና መቆራረጥ ዳይሬክቶሬቱ በሚሰራቸው ስጋት ስራ አመራር የማጠናከርያ ስራዎች በቀጣይ በእጅጉ በማሻሻል በማኑዋል የሚቀየር ስጋት ውሱን እንደሚሆን ይታመናል፡፡ ሆኖም በየቅ/ጽ/ቤቶች የስጋት ስራ አመራር ስራዎችን በማጠናከር ኦፐሬሽናል የሆኑ ስጋቶችን ለመቆጣጠር እና ወቅታዊ የሆኑ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ታሳቢ በማድረግ አገልግሎቱን ማፋጠን ያስፈልጋል፡፡ ሲስተም የጣለውን ስጋት ደረጃ በባለሙያዎች ጣልቃገብነት ማሻሻያ ማድረግ ሲያስፈልግ፣ በአውቶሜሽን ሲስተም የስጋት ደረጃ መጣል ሳይቻል ሲቀር ባለሙያዎች ስጋት እንዲጥሉ፣ ሲስተም በጣለው ስጋት ጣልቃ ገብተው እንዲያሻሽሉ የሚጋብዙ ሁኔታዎችና የጣልቃገብነቱ ደረጃ በዚህ ማኑዋል ተካትቷል፡፡

## 1.2. የተቋሙ ራዕይና ተልእኮ መግለጫ

ከተቋሙ የተመነዘረ የዳይሬክቶሬቱ ራእይ እና ተልእኮ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| | የተቋሙ | የዳይሬክቶሬቱ |
|---|---|---|
| ራዕይ | በ2012 በአፍሪካ ግንባር ቀደም የሆነ ዘመናዊና ፍትሐዊ የታክስ አስተዳደር ሰፍኖ አገራዊ ወጪ በአገራዊ ገቢ ተሸፍኖ ማየት፤ | ተቋሙ የዘመነ፤ ፈጣን፤ ፍትሓዊ እና ግልፀኝነት ያለው በአፍሪካ ምርጥ የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ስርዓት አፈፃፀም ያለው ሆኖ ማየት፤ |
| ተልዕኮ | ታክስና ቀረጥን በፈቃደኝነት የመክፈል ባህልን በማዳበር ህግን ሊያስከብር የሚችል ሙያዊ ብቃትና ተነሳሽነት ያለው ባለሙያ በመጠቀም፣ ዘመናዊ የታክስ እና ቀረጥ አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት፣ ለሃገር ልማት የሚውል ገቢ በብቃት በመሰብሰብ የዜጐችን ማህበራዊና ኢኮናሚያዊ ደህንነት ማረጋገጥ | ዘመናዊ፤ ግልጽነትና ተጠያቅነት ያለው የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ሥርዓት በመዘርጋት ተገልጋዮች ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፤ |
| እሴቶች | ደንበኛ ተኮር አገልግሎት መስጠት፤ የሕብረተሰቡን ደህንነት መጠበቅ ፤ከብልሹ ምግባር የፀዳ የስራ አካባቢ ፣ ሙያዊ ክህሎትን ለተጨባጭ ውጤት መጠቀም (Professionalism) ህግን ማስከበር ፤በቡድን መስራት ፤የሴቶችን ተሳትፎ ማረጋገጥ፤ | ዳይሬክቶሩቱ የተቋሙን እሴቶች ይተገብራል፤ |
| አላማዎች | ዘመናዊ የገቢ አወሳሰንና አሰባሰብ ሥርዓት በመዘርጋት ለተገልጋዮች ፍትሐዊ፣ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት መስጠት፣ታክስ ከፋዩ ግዴታውን በፍቃደኝነት እንዲወጣ ማስቻል፣ ኮንትሮባንድ፤ የታክስ ማጭበርበርና ስወራን በመከላከልና በመቆጣጠር የታክስና የጉምሩክ ሕግጋትን ማስከበር፣ ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን የታክስ ገቢ በብቃትና በወቅቱ መሰብሰብ፣ የፌዴራልና የክልል ታክስ አስተዳደር ሥርዓቶች የተጣጣሙ እንዲሆኑ ለማድረግ ለክልሎች አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ፤ | • የጉምሩክ የቁጥጥር እና የተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት አፈፃፀም የተጣጣመ ማድረግ፤<br>• ፈጣን ፍትሓዊ እና ቀልጣፋ የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር አገልግሎት ለመስጠት የጉምሩክና የታክስ ስነ ስረዓቱ በመረጃ ቴክኖሎጂ እንዲደገፍ ማድረግ እና<br>• ለልማታዊ ባለ ሀብቶች ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር፤ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቀሽ (AEO) ስርዓትን ማስፋፋት እና ማጠናከር፣<br>• በጉምሩክ አሠራር ላይ የሚታዩ ክፍተቶችንና ስጋቶች መለየት እና ማስተናገድ፣ አዳዲስ ስጋቶች የሚስተናገዱበት ሥርዓቶችን መቅረፅ፣ |

## 1.3. ዓላማ

የዚህ ማንዋል ዓላማ በሁሉም የጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤቶች የሚከናወኑ ስራዎችን በመለየትና እንዴት እንደሚሰሩ እንዲሁም ተጠያቅነትንና ኃላፊነትን በግልፅ በማስቀመጥ በየደረጃው ለሚገኙ ፈፃሚዎችና የስራ ሃላፊዎች የስጋት ደረጃን በተመለከተ የሚወስኑት ውሳኔዎች ወጥነት እና ግልጽነት ባለው መልኩ እንዲፈጸሙ ማስቻል ነው፡፡ በተለይ አውቶሜሽን ሲስተም የጣለው የስጋት ደረጃዎች ላይ ችግሮች ሲከሰቱ በማኑዋል ለማሸሻል እና አውቶሜሽን ሲስተም በተለያዩ ምክንያቶች የስጋት ደረጃ በማይጥልበት ጊዜ የስጋት ስራ አመራር ባለሙያዎች በጊዚያዊት ሲስተሙን ተክተው በማኑዋል የስጋት ደረጃዎችን ለመጣል የሚያስችል ዝርዝር አሰራር ለማስቀመጥ ያለመ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ማኑዋል የስጋት ስራ አመራር የስልጠና ስነድ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.4. አስፈላጊነት

የዚህ ማኑዋል አስፈላጊነት የስጋት ስራ አመራር መርህ በአዋጁና በፖሊሲው በጥቅል የተገለጸ በመሆኑ፤ ስጋት በባህሪው ተለዋዋጭ በመሆኑ እና አሰራሩን በመመርያ ለማስቀመጥ ስለማይቻል ፈጻሚዎች ስራዎቻቸውን በቀላሉ በግልጸነትና ተጠያቂነት ለማከናወን የሚረዳ መነሻ የአሰራር ማኑዋል ለማስቀመጥ ነው፡፡

## 1.5. የተፈጻሚነት ወሰን

ማኑዋሉ በማንኛውም የገቢ፣ የወጪ፣ የትራንዚት፣ የገቢ መንገደኞች እና የጉምሩክ ስነ-ስርዓት የሚፈጸምባቸው መቅረጫ ጣቢያዎችና ኤላዎች የሚፈጸም ሲሆን ለሀገር ውሰጥ ታክስ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

## 1.6. ትርጉም

**ስጋት፡-** የአንድ ተቋም ዓላማዎች እንዳይሳኩ የሚያደርጉ ውስጣዊና ውጫዊ አሉታዊ ክስተት(ቶች) ሲሆን ከጉምሩክ አንጻር ስጋቶች ዋጋ ማሳነስና ማብዛት፣ የታሪፍ ቁጥር ማሳሳት፣ የስሪት ሀገር ማሳሳት፣ የዕቃ መግለጫ ማሳሳት፣ በሰነድ ከተገለፀው ብዛት እና አይነት የተለየ ዕቃን ማምጣት፣ ኮንትሮባንድ፣ የቀረጥ ነጻና የመጋዘን እንዲሁም ሌሎች ልዩ መብቶችን አለአግባብ መጠቀም፤ ቀልጣፋ አገልግሎት አለመስጠት፣ አምራች ኢንዱስቲሪውን አለመደገፍ፣ የስነ-ምግባር ግድፈት የመሳሰሉ ናቸው፡፡

**የስጋት ስራ አመራር፡-** ስጋቶች ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የሚለዩበት፣ የሚተነተኑበት፣ የሚስተናገዱበት እና የሚገመገሙበት የስራ አመራር ጥበብ ሲሆን በዚህም ዕድሎች የሚለዩበት እና ሊፈጠር የሚችልን ኪሳራ እንዲቀንሱ ወይም እንዲወገዱ የሚደረግበት የአሰራር ዘዴ ነው፡፡ በተምሳሳይ በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 አንቀጽ ~~45~~ 6 መሰረት የስጋት ስራ አመራር ማለት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ፣በሚወጡና በሚተላለፉ ዕቃዎች ላይ አገልግሎት አሰጣጡንና የቁጥጥር ሥርዓቱን ሚዛናዊ ባደረገ ሁኔታ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የተለያየ የስጋት ደረጃ በማውጣት የሚከናወን የአሰራር ሥርዓት ነው፡፡

**የጉምሩክ ትራንዚት፡-** የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ያልተፈጸመበት ተላላፊ ዕቃ በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆኖ ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ ወይም ከመግቢያ በር እስከ መዉጫ በር በተፈቀደ መስመር የሚጓጓዝበት ሥርዓት ነዉ፡፡

**ካርጎ ስካኒንግ ማሽን፡-** ወደ ሀገር የሚገቡ ወይም ከሀገር የሚወጡ ተሽከርካሪዎች የያዟቸው ጭነቶች ወይም ከአገር የሚወጡ እና ወደ ሀገር የሚገቡ ጓዞች የሚፈተሹበት የዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ነዉ፡፡

**ቀይ ስጋት ደረጃ፡-** ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን በፍተሻ መመርያ መሰረት አካላዊ የዕቃዎች ፍተሻ እና የሰነድ ምርመራ እንዲደረግ የሚገልጽ መስመር (channel) ነው፡፡

**ቢጫ ስጋት ደረጃ፡-** መካከለኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን ሰነድ ምርመራ እንዲደረግ የሚገልጽ መስመር (channel) ነው፡፡

**አረንጓዴ ስጋት ደረጃ፡-** ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ማለት ሲሆን በመድረሻ ጣብያ የደረሱ ዕቃዎች የሰነድና የአካላዊ ፍተሻ ሳይደረግባቸው እንደደረሱ ተለቀው በድህረ- ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ቁጥጥር እንዲደረግባቸው የሚገልጽ መስመር ነው፡፡

**ብትኳናማ የስጋት ደረጃ፡-** ወደ ሀገር ውስጥ ሊገቡ ወይም ሊወጡ የተዘጋጁ ዕቃዎችን የጫኑ ተሽከርካሪዎች በከፍተኛ የስጋት ደረጃ ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ መስመር (channel) ሲሆን በስካኒንግ ማሽን/አካላዊ ፍተሻ እንዲደረግባቸው የሚገልጽ መስመር ነው፡፡

ነጭ ስጋት ደረጃ፡- ወደ ሀገር ውስጥ ሲገቡ ወይም ሲወጡ የተዘጋጁ ዕቃዎችን የጫኑ ተሽከርካሪዎች በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ ላይ መሆናቸውን የሚገልጽ መስመር (channel) ሲሆን በስካኒንግ ማሽን/አካላዊ ፍተሻ ሳይደረግባቸው እንዲለቀቁ የሚገልጽ መስመር ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የስጋት ስራ አመራር የአሰራር ፍሰት

## 2.1. የተግባራት ቅደም ተከተል (ደረጃዎች)

1ኛ. ስጋቶችን መለየት

2ኛ. መረጃ ማሰባሰብና ማደራጀት

3ኛ. ስጋትን መተንተንና የስጋት ደረጃ ማውጣት

4ኛ. የስጋት ደረጃ መጣልና ማሻሻል፤

5ኛ. የስጋት ደረጃዎች ውጤት መከታተል እና መገምገም፤

### 2.1.1. የመጀመሪያ ደረጃ:- ስጋቶችን መለየት፤

የተግባር መግለጫ

በየወቅቱ ሊከሰቱ የሚችሉ እና የተከሰቱ ስጋቶችን በቀጣይነት መለየት፤

አስፈላጊነት/Purpose

ስጋቶች እንዳይከሰቱ ከተከሰቱም በኋላ ከፍተኛ ችግር ሳያስከትሉ ለመቆጣጠር የሚያስችል አሰራር ለመንደፍና የስጋት ትንተና ለማከናወን ነው፡፡ ስጋት የመ/ቤቱ ግቦች እንዳይሳኩ የሚያደርግ ማንኛውም አሉታዊ ተጽኖ ሲሆን ዋናዋዎቹ የጉምሩክ ስጋቶች የሚባሉት ህገ-ወጥ ንግድ (ኮንተሮባንድ)፤ ንግድ ማጭበርበር፤ የዕቃዎች የስሪት ሀገር ማሳሳት፣ በመንግስት የተሰጡ መብቶች አለአግባብ መጠቀም፤ የተከለከሉና ገደብ የተደረገባቸው ዕቃዎች ማስገባት በአጠቃላይ በጉምሩክ አዋጅ 859/2006 መሰረት ሳይከናወን ሲቀር ስጋት ተከስቷል ሊባል ይችላል፡፡

የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

➢ *ከተለያዩ ስራ ክፍሎች ጋር ግኑኝነት መፍጠር ማለትም፡-*
  - ገቢና ወጪ ጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም፤
  - መጋዘን አስተዳደር ስራ ሂደት
  - ህግ ማስከበር ስራ ሂደት
  - ድህረ-ዕቃ አወጣጥ ስራ ሂደት፤
  - ጥናቶች ማካሄድ፤

- የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም የስራ ግምገማዎች ማድረግ፤
- የጉምሩክ አዋጅ፤ የተለያዩ መመርያዎች፤ ደንቦችና ፖሊሲዎችን መመርመር
- ከውስጥና ከውጭ ባለድረሻ አካላት ጋር የጋራና የተናጠል ውይይት ማድረግ፤
    - ✓ የውስጥ ባለድርሻ አካላት ሲባል በቅ/ጽ/ቤቱ ያሉ ፈጻሚዎችና ሃላፊዎች፤
    - ✓ የውጭ ባለድርሻ አካላት ሲባል በቅ/ጽ/ቤቱ ያሉ ተቆጣጣሪ መ/ቤቶች፣ ትራንዚተሮች እና ፈቃድ ሰጪ መ/ቤቶች ናቸው

*የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures*

- ➢ ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ያጋጠሙ ስጋቶችን መለየት፣
- ➢ የተለዩ ስጋቶችን ትክክለኛነታቸውን ማጣራት፤

## 2.1.2. ሁለተኛ ደረጃ፡- መረጃ ማሰባሰብ እና ማደራጀት፤

የተግባር መግለጫ

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ለስጋት ትንተና የሚያግዝ መረጃ መሰባሰብ፤

አስፈላጊነት/Purpose

ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች ለስጋት ስራ አመራር በሚጠቅም መልኩ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለስጋት ትንተና ግብአት ማዋል፤

*የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች*

- ➢ ተለይተው የተዘጋጁ ስጋቶች፤
- ➢ የተለዩ የመረጃ ምንጮች፤
- ➢ የተዘጋጁ መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች (በሲስተም ወይም በማኑዋል)


የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- ➢ ተለይተው የተቀመጡ ስጋቶችን ትክክለኛነታቸውን ቅድመ-ማጣራት ስራ ማከናወን፤
- ➢ የስራ ቅደም ተከተል ማዘጋጀት፤
- ➢ ከተለዩ የመረጃ ምንጮች መረጃ ማሰባሰብ፡-
    - በሲስተም የሚያዙ የሪከርድ መረጃዎች ከጉምሩክ ዳታ ቤዝ(አሲኩዳ)፣ ከስጋት ስራ አመራር ዳታ ቤዝ(TPRDP)፣ ECVS፣ VDD፣ SINGLE WINDOW ወዘተ፣

በየወቅቱ በሚያወጣው ቀመር መሰረት ይሰላል፡፡ ለምሳሌ ማኑዋሉ ሲዘጋጅ የነበረው ስሌት ≤10% LOW RISK, >10% AND ≤ 20% MEDIUM RISK, >20% HIGH RISK

- ✓ የተከሰተው ስጋት የሚያስከትለው ተጽኖ(CONSEQUENCE) ≤ 5% LOW RISK, >5% AND ≤ 7.5% MEDIUM RISK, >7.5% HIGH RISK ይሆናል፡፡

በመጨረሻም ሥጋት የመከሰት እድል (Likelihood) እና ሥጋቱ የሚያስከትለው የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ተጽእኖ (Consequence) ጥምረት (Matrix) በመስራት በሚከተለው ሰንጠረዥ መልኩ የመጨረሻውን የሥጋት ደረጃ ይወጣል፡፡




- ➢ የስጋት ደረጃ ማውጣት፡- የስጋት መረጃዎች ከተተነቱ በኋላ የስጋት ደረጃዎች ይወጣሉ፤
- ➢ የተተነተኑና የስጋት ደረጃዎች የወጡላቸው መረጃዎች ለውሳኔ ዝግጁ ማድረግና ለተጠቃሚ አካል ማስተላለፍ፡- በቅ/ጽ/ቤቱ የሚገኙ የተለያዩ ስራ ክፍሎች እና የስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት እንዲሁም ሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች የዚህ ውጤት ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡

### 2.1.4. አራተኛ ደረጃ፡ ስጋት መጣልና በሲስተም የተጣለ ስጋት ማሻሻል፤

### 2.1.4.1. የገቢ ዕቃ ስጋት አጣጣል፤

### 2.1.4.1.1. በሲስተም ስጋት መጣል በማይቻልበት ሁኔታ፡

*የተግባር መግለጫ*

በልዩ ልዩ ምክንያት ሲስተም በማይጥልበት ጊዜ ሲስተሙን ተክቶ በማኑዋል የስጋት ደረጃ መጣል፤

አስፈላጊነት/Purpose ፤

በተለያዩ ምክንያቶች የስጋት ደረጃ ሲስተም በማይጥልበት ጊዜ የሚፈጠርን የስራ መስተጓጎል ለማስቀረት፤

*የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች*

- በሲስተም ስጋት ደረጃ ያልተጣለበት ሰነድ፤
- የተደራጀ መረጃና የተተነተነ የስጋት ደረጃ ውጤት፤
- የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- በሲስተም የስጋት ደረጃቸው ያልተጣሉ ሰነዶችን ከፌዝቬት መቀበል፤
- የስጋት ደረጃዎችን ከዚህ በታች በተገለጸው (ሀ እስከ ሐ) መሰረት መጣል፤

ሀ) በአረንጓዴ/ሰማያዊ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

- የመንግስትና የመንግስት የልማት ድርጅቶች፤
- የልዩ መብት ተጠቃሚዎች፤
- ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች፤
- መብት ያለቸው ዲፕሎማቶች፤ ኤምባሲዎች፤ አለምአቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች፤

ለ) በቢጫ ስጋት ደረጋጃ የሚስተናገዱ፣

- ልዩ መብት ያልተሰጣቸው አምራች ድርጅቶች፣
- በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ምግቦች፤ተሰባሪና ጥንቃቄ የሚሹ ዕቃች(የታሸጉ ምግቦችን ሳይጨምር)፤
- የኢንቨስትመንትና የፕሮጀክት ማሽኔሪዎችና <u>የግብአት ዕቃዎች</u>፤
- የግብርና ግብዓቶች(ኬሚካሎች፣ዘሮች፣ማዳበርያዎች፣መረጫ መሳርያዎች ለምርምር የሚያገለግሉ የላቦራተሪ ዕቃዎች፤



Ethiopian ... Customs Authority ... No. 2

ሐ) በቀይ ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

- ከሶስተኛ ወገን የተገኘ መረጃ ሲኖር፤
- አሳመኝ የሆነ የከፍተኛ የስጋት አመላካች ሁኔታዎች ሲያጋጥም ለምሳሌ የእቃው አገላለጽ(የዕቃው መለኪያ በpcs መገለጽ ሲገባው በset ሲገለጽ፤ packing list invoice, bil of loading number ወዘተ በሚገባ ገላጭ ሳይሆን ሲቀር)፤
- ከሌሎች ቅ/ጽ/ቤቶች ወይም ኬላዎች ታጅቦ የተላከ ሲሆን፤
- ትኩረት የሚሻ ሪማረክ በመንገድ ወረቀት ላይ የተጻበት ከሆነ ( ለምሳሌ አስመጪ ስም ልዩነት ፤ የአመራች ሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖር ወዘተ)
- በዚህ ማኑዋል የተካተተው የስጋት ድግግሞሽና የሚያስከትለው ተጽኖ ስሌት መሰረት በከፍተኛ የስጋት ደረጃ በሚመደቡ አስመጪዎች፤

ከዚህ በላይ ከ(ሀ) እስከ (ሐ) ከተዘረዘሩት ሁኔታዎች ውጪ ሲያጋጥም ዳይሬክቶሬቱ የሚጠቀምባቸው የአውቶሜሽን ሲስተም መምረጫ መስፈርቶች መሰረት ስጋት ይጥላል፤ በአውቶሜሽን ሲስተም ሲሰራ የስጋት ደረጃቸው በማኑዋል የተጣሉ ሰነዶች በድጋሜ እንዲጣል ያደርጋል፡፡

ሲስተም የጣለው ስጋት ደረጃ በማኑዋል ከተጣለ ስጋት ደረጃ ልዩነት ሲኖር በማኑዋሉ የተጣለ ስጋት ደረጃ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 2.1.4.1.2. በሲስተም የተጣለ ስጋት በማኑዋል (manually) ማሻሻል፤

የተግባር መግለጫ

በአውቶሜሽን ሲስተም የሚጣልን የስጋት ደረጃ በማኑዋል ማሻሻል፤

አስፈላጊነት/Purpose

በአውቶሜሽን ሲስተም የሚጣል ስጋት ደረጃ ወቅታዊ የሆኑ ክፍተቶችን ግምት ውስጥ ያላስገባ (rulebased system) በመሆኑ በየጊዜው በማዕከል ደረጃ የስጋት ማሻሻያዎች ማድረግ በቂ አይደለም፡፡ በዋናው መ/ቤት በሲስተም አመካኝነት የሚጣሉ ስጋቶች ወቅታዊ (realtime situation) የሆኑ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን በተፈለገው ደረጃ ያገናዘበ ሊሆን ስለማይችል መሰል ክፍተቶችን እንደችግሩ ሁኔታ ለማስተዳደር በሲስተም የተጣለን ስጋት ጥራት መከታተልና በማኑዋል መሻሻያዎችን ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- በሲስተም የስጋት ደረጃ የተጣለበት ሰነድ፤
- የተደራጀ መረጃና የተተነተነ የስጋት ደረጃዎች፤
- የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- በሲስተም የስጋት ደረጃቸው የተጣሉ ሰነዶችን ከፌዝቬት መቀበል፤
- ስጋቶችን ከዚህ በታች በተገለጸው(ሀ እስከ ሐ) መሰረት ማሻሻል፤

ሀ) ከቢጫ ወይም ከቀይ ወደ አርንጓዴ/ሰማያዊ (AEO) ማሻሻል፤

አውቶሜሽን ሲስተም የጣለው ስጋት ደረጃ ከቢጫ ወይም ቀይ ወደ አርንጓዴ ወይም ወደ ሰማያዊ በቀጥታ ማሻሻል የሚቻለው የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው፡፡

- ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ ድርጅቶች (Special Privilege scheme)፤ (በ 'S' የሚመጡ ሰነዶችንም ጨምሮ)፤
- የቫውቸር እና የኤክስፖርት ቦንድድ መጋዘን ተጠቃሚዎች (የሚያስገቡት ዕቃ ጥሬ ዕቃ በመሆኑና ኤክስፖርት ዕቃዎች በማምረት የተሰማሩ ስለሆነ)፤
- መንግስት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ በልዩ ሁኔታ በቀረጥ ነጻ በCPC 421 የሚስተናገዱ ዕቃዎች፤
- በተመረጡ ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽነት መብት በተሰጣቸው ድርጅቶች (AEO) የሚገቡ ዕቃዎች፤ (በ 'S' የሚመጡ ሰነዶችንም ጨምሮ)፤
- የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች CPC 4000/403፣ 4000/401፣ 4000/410፣ 4000/441 የመጠቀም መብት ያላቸው ሆነው በራሳቸው ስም ሲያስመጡ፤
- ዲፕሎማቶች፤ ኤምባሲዎችና አለም አቀፍ ድርጅቶች CPC 415፤476፤473፤
- ለኤግዚቢሽን የሚገቡ ዕቃዎች (አስቸኳይ ከመሆናቸው በተጨማሪ ንግድን ለማስተዋወቅ ተጋብዘው የሚመጡ ስለሆነ)፣CPC 414

ለ) ከአረንጓዴ ወይም ከቀይ ወደ ቢጫ የሚሻሻሉ፤

- ሰነዱን በመመርመር ስጋቱን መቆጣጠር የሚቻል ሲሆን (ለምሳሌ የዋጋና ታሪፍ ችግር ያለው ሆኖ ያለፍተሻ ማስተናገድ ሲቻል)፤

- በንድድ መጋዘን የተፈቀደላቸው አስመጪዎች ሰነዶቻቸው ከ'S' ወደ 'C' ሲቀየር (በሚቀናነስበት ጊዜ ተጨማሪ ክፍያ ሲኖር ሰነድ መርማሪው እንዲያረጋግጥ)፤
- በቀላሉ በአይን በማየት ሊለዩ የሚችሉ ትላልቅ ማሽኔሪዎች፤ የፕሮጀክት ዕቃዎች፤ (excavator, drilling machines, lease machines, agricultural machinaries etc)
- የአለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም የኤምባሲዎች ተሽከርካሪዎች በሚያስመጡበት ጊዜ (ይህም ተሽከርካሪዎች ወደ ሦስተኛ ወገን በሚተላለፉበት ጊዜ የዋጋ ትክክለኛነት አረጋግጦ ለማስተላለፍ ስለሚያግዝ ነው)፤
- የስም ዝውውር የሚከናወንባቸው ሰነዶች (CPC code 442, 443, 450, 485, 487, 488, 489, 490, 491, 492, 494, 495 ወዘተ)
- ቀረጥ የሚከፈልበትና የማይከፈልበት ዕቃ በአንድ ሰነድ ተቀላቅለው ሲመጡ፤
- ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች፤
- የሁለተኛ መደብ (second schedule) ተጠቃሚ አምራቾች፤
- ኬሚካሎች፣ መድሃኒቶች፤ በቀላሉ ሊበላሹ የሚችሉ ልዩ ልዩ ዕቃዎች (ዋጋቸው በመጠንና ቲክነስ የሚወሰኑትን ለምሳሌ እንደ ሲራሚኮችን ሳይጨምር)፣ የህክምና መገልገያ መሳርያዎችና ምግቦች (በቀላሉ የማይበላሹ የታሸጉ ምግቦችን ሳይጨምር)፤
- ብረታ ብረቶች (አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አልፎ አልፎ ክብደት እየተረጋገጠ)፤
- ተቀጣጣይ (explosive goods) እና ጨረር አመንጪ ዕቃዎች፤
- ሌሎች በቀላሉ በሙቀት እና በአያያዝ ሊበላሹ የሚችሉ ዕቃዎች(ማስጠንቀቂያ ምልክት የተጻፈባቸው)፤

ሐ) ከአረንጓዴ ወይም ከቢጫ ወደ ቀይ የሚሻሻሉ፤

በአረንጓዴና በቢጫ ስጋት ደረጃ የተመረጡ ሰነዶች በቀጥታ ወደ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ ለማሻሻል ሲያስፈልግ ቀጥለው ከተዘረዘሩት ነጥቦች ቢያንስ አንዱ ሲያሟላ ነው፤

- ከከፍተኛ ስጋት ደረጃ የተመደቡ ሀገራት የሚመጡ ዕቃዎች ሆኖው በዓይነት፤ በቲክነስ፤ በጥራት፣ በመጠን፣ በብራድ፣ በቀለመም ወዘተ መሰረት የሚወሰኑ

በዋጋ ማነጻጸርያ ላይ ከተጠቀሱ ዕቃዎች ሲነጻጸሩ ከፍተኛ የሆነ የዋጋ ልዩነት ሊያስከትል የሚችሉ ዕቃዎች ሲሆኑ፤

- አዲስ አስመጪ ከሆነ (ማስመጣት ከጀመረበት ቀን ጀምሮ ሦስትና ከሦስት ጊዜ በታች ሲያስመጣ)፣
- ቦንድድ መጋዘን የተፈቀደላቸው አስመጪዎች በ'S' ዲክሌር ሲያደረጉ (ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ እና የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚ ድርጅቶችን ሳይጨምር)፤
- የሰነዶች (ኢንቮስ ወይም ቢዲዲ) አገላለጽ ለዋጋና ታሪፍ አወሳሰን በሚመች መልኩ ያልቀረበ ሲሆን፤ ሰነድ መርማሪ ኦፊሰር ጥያቄ ሲያቀርብ፤
- አስመጪው በመረጃ ቋት (tprdp system) እና በማኑዋል ከሚያዙ መረጃዎች መሰረት በተደጋጋሚ የፍተሻ ልዩነት የተያዘበት ሆኖ ስጋት ደረጃው በሲስተም ካልተሻሻለ (Likelihood >20% and Consequence > 7.5%) ፤
- ከሶስተኛ ወገን የተገኘ መረጃ (ጥቆማ) ሲኖር፤
- ከሰነድ መርማሪ ወይም ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ዕቃው እንዲፈተሽ ጥያቄ ሲቀርብ፤
- ልዩ መብት የተሰጣቸውና ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶችም በሲስተም በአረንጓዴና በቢጫ ስጋት ከሚስተናገዱ ሰነዶች ውስጥ አምስት በመቶውን ወደ ከፍተኛ ስጋት ደረጃ በመቀየር ድንገተኛ (surprise checking) ፍተሻ እንዲከናወንበት ማድረግ፤ -ሲስተም የሚጥለው አልፎ አልፎ መረጣ (Random Selection) ከአጠቃላይ አስመጪዎች በመሆኑ የእያንዳንዱን አስመጪ የህግ ተገዥነት ደረጃ ለማወቅና አዳዲስ ስጋቶችን ለመለየት በቂ ስላልሆነ፤
- የውጭ ፍተሻ የተፈቀደላቸው አስመጪዎች ሆነው፤ አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ( ልዩ መብት የተሰጣቸው፣ ታማኝ የኢኮኖሚ እንቀሳቃሽ፣የመንግስትና የልማት ድርጅቶች ሳይጨምር)፤
- በጉምሩክ መጋዘኖች ጉምሩክ ስነስርዓት የሚፈጸምባቸው ተሽከርካሪዎች (የመንግስትና የልማት ድርጅቶች ሳይጨምር)፤
- በጊዜያዊት የሚገቡ ዕቃዎች (ዲፕሎማቲክ መብት ካላቸው ውጪ)፤
- ከተጓዳኝ መ/ቤቶች ቅድመ-ሁኔታ ተሟልቶ እንዲስተናገዱ ከተገለጸ (ለምሳሌ ቀረጥ ነጻ ተፈቅዶላቸው ቅድመ-ሁኔታዎች ተረጋግጠው እንዲስተናገዱ የሚጠይቅ ደብዳቤ ሲኖር እና ወ.ዘ.ተ)፤

- በክፍልፋይ ተጓጉዘው የሚመጡ ጭነቶች (partial shipment) አጠራጣሪ ሁኔታ ሲያጋጥም (ጥቆማ፤ ሪማርክ ወዘተ ሲኖር)፤
- ልዩ መብት የተፈቀደላቸው ድርጅቶች ዘርፉን ከሚገልጽ የአስመጭነት የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር የመጨረሻ ኮድ ውጪ ሲያስመጡ፤ ዕቃው ከተፈቀደለት ዓላማ ውጪ ይውላል ተብሎ ሲታመን እና አጠራጣሪ ሁኔታዎች ሲኖሩ፤
- አሃጉራዊና አለም አቀፍ ድርጅቶች፤ ልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች፤ ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች እና የመንግስት መ/ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ዕቃዎች በሌላ ስም (careoff) ሲመጡ፤
- በአካል የተገኘ የአምራቹ የኮንቴር ሲል ቁጥርና በሰነድ ላይ ከተጠቀሰው የሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖረው፤
- ለጥገና ወደ ውጪ ወጥቶ በIM6 የሚገቡ ዕቃዎች ሲሆኑ፤
- በሚሚያ እና በምትክነት የሚገቡ ዕቃዎች ሲሆኑ እና ኤክስፖርት ተደርገው በተለያየ ምክንያት ወደ ሀገር ተመልሰው ሲገቡ (በብልሽት፣ በጥራት መጓደል ወ.ዘ.ተ)፤
- ያገለገሉ ዕቃዎች (used goods) ከትላልቅ ማሽነሪ ዕቃዎች ውጪ ሲሆን፤
- ተመላሽ ኢትዮጵያውያን የሚያስመጡዋቸው ዕቃዎች፣
- ተሽከርካሪዎች (የአለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች እንዲሁም የኤምባሲዎች ከሚያስመቸው ውጪ)፤
- 60% እና በላይ ኤክሳይስ የሚጣልባቸው ዕቃዎች (በልዩ ሁኔታ መብቱ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ)፣
- በአንድ ኮንቴነር ከሁለት በላይ አስመጪዎች ስም ሲመጣ(PART CONTAINER)፤ (በልዩ ሁኔታ መብቱ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ውጪ)፤

## 2.1.5. የገቢና ወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ስጋት ደረጃ አጣጣል፤

### 2.1.5.1. የገቢ ትራንዚት

የተግባር መግለጫ

የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥርን በስጋት ስራ አመራር መሰረት ማከናወን፤

### *አስፈላጊነት/Purpose*

የገቢ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥር በካርጎ ስካኒንግ መፈተሻ መሳርያ እየታገዘ በማከናወን ቁጥጥሩን ውጤታማ በሆነ መልኩ ለማረጋገጥ በስጋት ስራ አመራር መሰረት ተግባራዊ ለማድረግ፤

የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- በትራንዚት ኢንስፔክተር የተረጋገጠ የመንገድ ወረቀት (T1)፤
- የትራንዚት ዲ/ዮን (IM8)፤
- ትራክ ማንፌስት፤
- የተደራጀ የስጋት መረጃ፤
- የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

### *የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures*

- ሰነድ ከትራንዚት ቁጥጠር ባለሙያ መቀበል፤
- ስጋቶችን ከዚህ በታች በተገለጸው(ሀ እስከ ለ) በመጣል ወደ ሚቀጥለው ስካኒንግ ዩኒት ማስተላለፍ፤

ሀ) በከፍተኛ (ብርቱካናማ) የስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

- ከኢተለጀንስና ከተለያዩ አካላት ጥቆማ የሚቀርብባቸው፤
- የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት ከሌላቸው ሀገራት የተመረቱ ወይም የተጫኑ ከሆነ (ለምሳሌ ሶማሊያ፣ ሲሪያ፣ አፍጋኒስታን፣ ኮንጎ፣ ሱዳን፣ የመን፣ ሊቢያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ኢራክ፣ እና የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሮክቶሬት በሚልካቸው መረጃዎች መሰረት)፤
- በአደንዛዝ ዕጽ ዝውውር ከታወቁ ሀገራት የተጫኑ ከሆነ (ለምሳሌ አፍጋኒስታን፣ ፓኪስታን፣ ኮሎምቢያ፣ ሜክሲኮ፣ ታይላንድ፣ ናይጀሪያ እና የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሮክቶሬት በሚልካቸው መረጃዎች መሰረት)፤

- በመንገድ ወረቀቱ ላይ ጨረር አመንጪ ዕቃዎች የተገለጹ ከሆኑ፤
- በመንገድ ወረቀቱ (T1) ላይ ሪማርክ የተፃፈ ከሆነ፤
- ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ሲመጡ በግልጽ በማየት መለየት የማይቻሉ ከሆነ (ከታች በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የተመደቡትን ሳይጨምር)፤
- ዕቃዎች ካላቸው ባህሪ አንጻር የማጭበርበር ድርጊት የሚፈጸምባቸው በየወሩ በፍተሻ እና ሰነድ ምርምራ ሪፖርት የቀረበባቸው፤ /ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል ከሚገኙ መረጃዎች/
- ሶስት እና ከዚያ በላይ የከባድ ጥፋት ሪከርድ ባለባቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አስፈጻሚዎች የሚስተናገዱ ሰነዶች፤ /ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል ከሚገኙ መረጃዎች/
- የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና የታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች (AEO) ዕቃዎች ከሌሎች ጭነቶች ጋር ተቀላቅለው ሲመጡ፤
- በሚያዙ የጥፋት መረጃ መሰረት በተደጋጋሚ የአገላለጽና የትርፍ ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ሲያስመጡ፤ ወይም በተደጋጋሚ የሰነድ ምርመራ፣ የፍተሻ እና የድህረ ዕቃ አወጣጥ ግኝት የሚገኝባቸው አስመጭዎች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች፤ (ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል በተያዙ መረጃዎች መሰረት)
- ከጭነቱ ጋር የማይሄድ የተጋነነ ትራንስፖርት ወጪ፤ (ከዕቃው ጋር ተመጣጣኝ ያልሆኑ የትራንስፖርት ክፍያዎች መኖሩ ሲረጋገጥ)፤
- ተሽከርካሪው ከሚጠበቅበት ጊዜ በላይ ዘግይቶ ሲደርስና አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ፤
- መኪናው በተነሳበት ሁኔታ የደረሰ ካልሆነና አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር (ሲሉ የተበጠሰ ከሆነ)
- የንግድ እቃዎች በብትን ጭነቶች ሲመጡ፤
- የሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖር፤
- በክፍልፋይ የሚጓጓዙ ጭኖቶች፤

ለ) በዝቅተኛ (ነጭ) ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፤

- ትላልቅ ወይም ግዙፍ እቃዎች ሆነው በአይን በማየት ብቻ የሚለዩ (የፋብሪካና የፕሮጀክት ማሽነሪዎች እና ዕቃዎች)፣
- በመንግስታዊና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚገቡ ዕቃዎች፣
- በትምህርት ተቋማት የሚገቡ የትምህርት መገልገያ መሳርያዎች፤
- በታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች (AEO) የሚገቡ ዕቃዎች፣
- በቬና ኮንቬንሽን እና በሌሎች ስምምነቶች መሰረት ያለመፈተሽ መብት የተሰጣቸው ሲያስመጡ፣
- በጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጣቃሚ የሆኑ አምራች ድርጅቶች የሚገቡ፣
- ክፈት ጭነቶች ሲመጡ በማየት ብቻ ማለፍ የሚችሉ ከሆነ፤

## 2.1.5.2. የወጪ ትራንዚት፤

የተግባር መግለጫ

የወጪ ዕቃዎች ትራንዚት ቁጥጥርን በስጋት ስራ አመራር መሰረት ማከናወን፤

አስፈላጊነት/Purpose

ሀገሪቱ ወደ ውጭ የምትልካቸው ምርቶች ጥራታቸውን ጠብቀው መውጣታቸውን እና ከተለያዩ ባዕድ ነገሮች ነጻ መውጣታቸውን ለማረጋገጥ፤

የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- በትራንዚት ኢንስፔክተር የተረጋገጠ የመንገድ ወረቀት (EX1)፤
- የትራንዚት ዲ/ዮን (EX1)፤
- የተደራጀ የስጋት መረጃ፤

*የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures*

- ሰነድ ከትራንዚት ቁጥጥር ባለሙያ መቀበል፤
- ሁሉም በብርቱኳናማ ስጋት ደረጃ ተመድበው በመውጫ በሮች የእየተረጋገጡ ማስተናገድ፤

## 2.1.6. የገቢ መንገደኞች የስጋት ደረጃ አጣጣል፤

የተግባር መግለጫ

ገቢ መንገደኞችን በስጋት ስራ አመራር መሰረት ማስተናገድ፤

*አስፈላጊነት/Purpose*

የገቢ መንገደኞችን መስተንግዶ የተመጣጠነ ቁጥጥርና የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲኖር ለማድረግ፤

*የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች*

- ቅድመ-መረጃ (prearrival manifest)፤
- የተደራጀ የስጋት መረጃ (የመንገደኞች የኋላ ታሪክ)፤
- የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

*የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures*

- ቅድመ-መረጃ (prearrival manifest) ከአየር መንገድ፤ ከመንገደኛው፤ ወዘተ መቀበል፤
- መረጃውን መተንተን፤
- መንገደኛው ከመድረሱ በፊት ወይም መድረሱ ሲረጋገጥ ስጋቶችን ከዚህ በታች በተገለጸው(ሀ እስከ ለ) መሰረት በመጣል ለቀጣይ ስራ ማስተላለፍ፤

ሀ) በዝቅተኛ (አረንጓዴ) ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ

- በዝቅተኛ ስጋት ደረጃ ላይ ከተመደቡ ሀገራት ለጉብኝት፤ ለአለምአቀፍና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎች ወይም ለኮንፈረስ የሚመጡ፤
- ለነጻ ህክምና አገልግሎት፤ ለሰብአዊ እርዳታ እና የትምህርት አገልግሎት ለመስጠት የሚመጡ፤
- ዲፕሎማቲክ መብት ያላቸው መንገደኞች፤
- ለጥናትና ምርምር የሚመጡ መንገደኞች፤
- በመንግስታዊ እና በግል ተቋማት ለተለያዩ አገልግሎቶች ተጋብዘው የሚመጡ መንገደኞች፤
- ተመላሽ ኢትዮጵያውያን፤
- ለመጀመርያ ጊዜ የሚመጡ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ-ኢትዮጵያውያን፤

- የመንግስትና የግል ተቋማት ሰራተኞችና ሃላፊዎች ስልጠና፣ ኮንፈረንስ፣ ዎርክሾፖች ወይም ሴሚናሮች ተሳትፈው የሚመለሱ፣
- በኢትዮጵያ በኩል ወደሌሎች ሀገሮች ትራንዚት የሚያደርጉ ሆነው ለአጭር ጊዜ የሚቆዩና ከኤርፖርቶች የማይወጡ ሲሆን፣ (በሀገር ውስጥ ቆይታ የሚያደርጉትን ሳይጨምር)፣

ለ) በከፍተኛ (ቀይ) ስጋት ደረጃ የሚስተናገዱ፣

- የጉዞው ዓላማ ለንግድ ከሆነ፣
- የማንኛውንም ድርጅት ዕቃ ይዘው የሚመጡ መንገደኞች (ከድፕሎማቶች ውጭ)፣
- ተመላላሽ መንገደኛ(በሦስት ወር አንድ ጊዜና ከዛ በላይ) በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ውጭ ሀገር ወይም በሀገር ውስጥ የሚመላለስ፣
- ከዚህ በፊት ሪኮርድ የተያዘበት መንገደኛ፣
- የጉዞው መነሻ ሀገራት ከከፍተኛ ስጋት ደረጃ ያላቸው ሀገራት ሲሆን፣
- የተቆጣጣሪ መ/ቤቶች ፈቃድ የሚጠይቅ ዕቃ የያዘ መንገደኛ፣
- ለኤግዚቪሽን ጉዳይ ምርትና አገልግሎት ለማስተዋወቅ እና ለማዘጋጀት የሚመጡ፣
- በግል ጉዳይ ከሀገር ወጥተው የሚመለሱ፣
- ከፍተኛ የስጋት ደረጃ ካላቸው ሀገሮች ተላልፈው (through transit) የሚመጡ፣
- በዝቅተኛ ስጋት ደረጃ እንዲስተናገዱ የተዘረዘሩት ዲፕሎማቲክ መብት ካላቸው መንገደኞች ውጪ አምስት በመቶ በራንደም መረጣ፣
- የመንገደኛው የትውልድ ሃገር በከፍተኛ ስጋት ደረጃ የሚመደብ ሲሆን
- የመንገደኛው የተለየና ያልተለመደ አካለዊ እንቅስቃሴ ሲያሳይ (ለምሳል መነጫነጭ፣ ያልተለመደ ላብ፣ ቅብጥብጥነት፣ ሚዛን ጠብቆ ያለመሄድ ወዘተ)
- ከሦስተኛ ወገን መረጃ ሲገኝ፣
- መንገደኞች ይዘውት የሚመጡት ጥቅል ከሚመጡበት ዓላማ አንጻር ብዛት ሲኖረው (ለምሳሌ ለትምህርት ወይም ለስብሰባ ሄዶ ሲመለስ ብዛት ያላቸው ሻንጣዎች ሲይዝ/ስትይዝ)፣
- በኢትዮጵያ በኩል ወደሌሎች ሀገሮች ትራንዚት የሚያደርጉ መንገደኞች ሆኖው በሀገር ውስጥ ቆይታ የሚያደርጉ ሲሆን፣
- መንገደኞች ይዘዋቸው በሚመጡ ዕቃዎች ላይ የጥርጣሬ ሪማርክ የተደረገበት፣ ከኢንተለጀንስ እና ከሌሎች አካለት የጥርጣሬ መረጃ የቀረበበት ሲሆን፣

## 2.1.7. ጉምሩክ መጋዘን ድልድል፤

የተግባር መግለጫ

ዕቃዎችን ለፍተሻ አመቺ በሆነ ሁኔታ ስጋትን መሰረት ያደረገ የመጋዘን ድልድል ማድረግ፤

አስፈላጊነት/Purpose

እቃዎች በባህሪያቸውና ሊከተል የሚችልን ስጋት መሰረት በማድረግ ሲደለደሉ ውጤታማ የሆነ ፍተሻ ለማከናወን እና ዕቃዎች ሳይሰባበሩ በፍጥነት ለማስተናገድ፤

*የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች*

- የትራንዚት ሰነድ መቀበል፤
- የተደራጀ መረጃ፤

*የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures*

- የትራንዚት ሰነድ መቀበል፤
- በዕቃዎች ባህሪ እና በአስመጪዎች ፕሮፋይል መሰረት መጋዘን ድልድል ከዚህ በታች በተገለጸው (ሀ እስከ ሐ) መሰረት ይከናወናል፤

ሀ) በዝግ መጋዘን የሚስተናገዱ ዕቃዎች

- የመለዋወጫ ዕቃዎች፤
- የተዘጋጁ ልብሶች፤ የተለያዩ ጨርቃጨርቆችና የጨርቃጨርቅ ውጤቶች እና ጫማዎች፤
- አሻንጉሊቶችና ማጫወቻ ዕቃዎች፤
- በኮንቴነር ተጭነው የሚመጡ ሦስተና ከሦስት ዓይነት ዕቃዎች በላይ (እንደየእቃዎች ዓይነትና ባህሪ፣ የአስመጭዎች መብት እየታየ የሚስተናገዱ ይሆናል)፤
- ጎማጎጦች፤
- በአንድ ጭነት ወይም ኮንቴነር ሁለት እና ከዚያ በላይ ዲክላሬሲዎኖች ይዘው ሲመጡ፣ (እንደ ዕቃዎቹ ባህሪ ታይቶ ይወሰናል)

ለ) በክፍት መጋዘን (Container Free Space) የሚስተናገዱ ዕቃዎች፤

- ፕላስቲኮችና የፕላስቲክ ውጤቶች፤
- ኤሌክትሮኒክስ፤
- የታሸጉ ምግቦችና መጠጦች (ጁሶች፣ ቸኮሌቶች፣ ከረሜላዎች፣ ማስቲካዎች፣ ዊስኪዎች ወዘተ)፤
- የህንጻ መሳርያዎች (ሴራሚክ፣ መስተዋቶች፣ አምፖሎች ወዘተ)፤
- የተለያዩ የቤትና የቢሮ መገልገያ ዕቃዎች፤
- የጽህፈት መሳርያዎች፤
- የመዋብያና የንጽህ መጠበቂያ ዕቃዎች፤
- የተለያዩ ምንጣፎች፤
- ኮምፒተሮችና የኮምፒተር አክሰሰሪ ዕቃዎች፤
- ሞተር ሳይክሎችና ብስክሌቶች፤
- ተለያይተው የሚመጡ የመኪና አካላት፤

ሐ) በትራክ (ከተሽከርካሪዎች ሳይራገፉ) የሚስተናገዱ(በዩኒ ሞዳል የሚስተናገዱ)፤

- ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳሾች፣ ልዩ መብት ተጠቃሚዎች፣ የመንግስትና የመንግስት የልማት ድርጅቶች፣ ዲፕሎማቶች፣ አለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶችና ኤምባሲዎች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች፤
- መድሃኒቶች፣ ጎማዎች፣ ብረታብረቶችና፣ ኬሚካሎች፣ በቀላሉ የሚበላሹ ምግቦች፤
- የፋብሪካ ግብአቶችና ድጋፍ ሰጪ ዕቃዎች፤
- ማሽኔሪዎችና የፕሮጀክት ዕቃዎች፤
- ተቀጣጣይና አደገኛ ዕቃዎች፤
- ወረቀቶችና የወረቀት ጥሬ ዕቃዎች፤
- በቀላሉ የሚበላሹና ተሰባሪ ዕቃዎች (ከአምስት አይነት በላይ ካልሆኑ)፤
- የተለያዩ የግብርና ግብአቶች፤
- የግብርና ውጤቶች፤

ማስታዎሻ፡-

1. ተሽከርካሪዎች በተመደበላቸው መጋዘን ይስተናገዳሉ፡፡

2. በዩኒሞዳል ተጓጉዘው የሚመጡ ጭነቶች መጋዘን ድልድል ተከናውኖባቸው የስጋት ደረጃቸው ከተወሰነ በኋላ የተመደቡበትን መጋዘን ማሻሻል ይቻላል፡፡

3. በመልቲ ሞዳል (ትራክ መጋዘን ለሌላቸው) ተጓጉዘው ለሚመጡ ጭነቶች በትራክ እንዲስተናገዱ የተዘረዘሩት በሲኤፍሲ መጋዘን ይስተናገዳሉ፡፡

4. ከላይ ከሀ እስከ ሐ ከተጠቀሱት ውጭ ዕቃዎች በሚመጡበት ወቅት እንደየ ዕቃዎቹ ባሕሪና እንደ ስጋት ደረጃ መሰረት እየታየ በመጋዘን የስራ ሂደት/ቡድን መሪ የመጋዘን ድልድል ይከናወናል፡፡

## 2.1.8. የወጪ ዕቃዎች ስጋት አመዳደብ፣

***የተግባር መግለጫ***

*የወጪ ዕቃዎች ቁጥጥርን በስጋት ስራ አመራር መሰረት ማከናወን፣*

አስፈላጊነት/Purpose

*በወጪ ዕቃዎች ላይ ስጋትን መሰረት ያደረገ ቁጥጥርና የተቀላጠፈ አገልግሎት ተግባራዊ ለማድረግ፣*

የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች

- ➢ በፊስቬት ተቀባይነት ያገኘ ሰነድ፣
- ➢ የተደራጀ መረጃ፣
- ➢ የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፣

የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures

- ➢ ሰነዶችን ከፊዝቬት መቀበል፣
- ➢ ስጋቶችን ከዚህ በታች በተገለጸው(ሀ እስከ ሐ) መሰረት መጣል፣

### ሀ)ዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ፣

- ልዩ መብት ተጠቃሚ አምራች ድርጅቶች የሚልኩዋቸው ዕቃዎች፣
- ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርቶች የሚልኳቸው ዕቃዎች፣
- መንግስታዊ እና የመንግሰት የልማት ድርጅቶች የሚልኳቸው ዕቃዎች፣
- አለማቀፍና አህጉር አቀፍ ድርጅቶች፣ ኤምባሲዎች እና ዲፕሎማቶች የሚልኳቸው ዕቃዎች( ለምሳሌ ተመላሾች)፣

## ለ) በመካከለኛ ስጋት ደረጃ የሚመደቡ፤

- የቁም እንስሳት፣
- ጫት፣ ቡና፣ አበባ፣ የቅባት እህሎች፣ ቅመማ ቅመሞች፣
- ቆዳ፣
- ሌሎች የተንዳኝ መ/ቤቶች ፈቃድ የሚጠየቅባቸው ዕቃዎች፣

## ሐ)በከፍተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ፤

- ለጥገና ወደ ውጭ የሚላኩ ዕቃዎች፤
- በጊዜያዊነት ገብተው የነበሩት ዕቃዎች ሲመለሱ፤
- ታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ድርጅቶች የሚልኳቸው ዕቃዎች አልፎ አልፎ(አምስት በመቶ እየታዬ)፤
- የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚልኳቸው ዕቃዎች አልፎ አልፎ (አምስት በመቶ እየታየ)፤
- በተለያዩ ምክንያቶች ወደ መጡበት ሀገር እንዲመለሱ የሚደረጉ ዕቃዎች፤
- ኤክስፖርት በሚያደርጉበት ጊዜ በተደጋጋሚ የፍተሻ ልዩነት በሚገኝባቸው ላኪዎች፤
- ከሶስተኛ ወገን መረጃ ሲገኝ፤
- ከሰነድ መርማሪ ወይም ከተለያዩ የስራ ክፍሎች ዕቃው እንዲፈተሽ ጥያቄ ሲቀርብ፤

<u>ማስታዎሻ፡-</u>

በወጭ ዕቃዎች ላይ የተጣለው የስጋት ደረጃ እንደተጠበቀ ሆኖ የሁሉም ወጭ ዕቃዎች ሰነድ እየተመረመረ ይስተናገዳሉ፡፡

የኢትዮጵያ ... ጉምሩክ ባለሥልጣን ... ቤት ...

## 2.1.9. ደረጃ አምስት፡ የስጋት ደረጃዎችን ውጤት መከታተልና መገምገም

*የተግባር መግለጫ*

*የስጋት ደረጃዎች ከተጣሉ በኋላ ውጤታቸውን መከታተልና መገምገም፤*

*አስፈላጊነት/Purpose*

*የስጋት ደረጃዎች ከተጣሉ በኋላ ውጤታቸውን መከታተልና በመገምገም በማኑዋል የጣሉ ስጋቶችን መቀነስ፤የሲስተም ክፍተቶችን በቀጣይነት ለማሻሻል እና ህግ ተገዥነት ደረጃ ለማሳደግ፤*

*የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች*

- የተደራጀ መረጃ፤
- የስጋት ስራ አመራር መሰረታዊ ክህሎት፤

*የአፈፃፀም ቅደም ተከተል/ Procedures*

- በሲስተምና በማኑዋል የተሰበሰቡ መረጃዎችን ማዘጋጀት፤
- ስጋቶችን ከዚህ በታች በተገለጸው መሰረት ውጤቱን መገምገምና ሪፖርት ማረግ፤
  - ስጋት ከተጣለ በኋላ ውጤታማነቱን በመከታተል የስጋት ደረጃዎች ማሻሻያ ለማድረግ መረጃዎች በመተንተን ለማዕከል ሪፖርት ማድረግ፤
  - የህግ ተገዥነት ችግር ያለባቸው ደንበኞች በቅ/ጽ/ቤት ደረጃ በመለየት አስፈላጊው ድጋፍና ስልጠና መስጠት፤ በልዩ ሁኔታ ከፍተኛ ጥፋት ያለባቸው ደግሞ በወቅቱ በመለየት ለሚመለከተው አካል(ስራ ክፍል) ሪፖርት ማድረግ፤
  - በስጋት ስራ አመራር አመካኝነት የተጣሉ ስጋት ደረጃዎች አፈጻጸማቸውን በመከታተልና በመገምገም ውጤታማነታቸው ማረጋገጥ፤
  - የቁጥጥር እና የተሳለጠ አገልግሎት አሰጣጥ የተመጣጠነና ውጤታማ መሆኑ በየወቅቱ በመገምገም እንዲሻሻል ማድረግ፤
  - የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አፈጻጸም ውጤት (የፍተሻ፣ ሰነድ ምርመራ፣ ትራንዚትና መጋዘን ቁጥጥሮች) እንዲሁም የድህረ-ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ውጤት በተመለከተ የሚያዙ መረጃዎች በተፈለገው ጥራት ደረጃ መያዛቸውን መከታተል ፤
  - የመረጃ ቋት ሲስተም ውጤታማ እንዲሆን ክትትል ማድረግ፣ ስልጠና መስጠት እና የማሻሻያ ጥናት ማድረግ፤

ማስታወሻ:-

- የስራ ሃላፊነትን በተመለከተ በስራ መዘርዝር ላይ በተቀመጠው የሃላፊነት ደረጃ መሰረት በየደረጃው ባሉ ባለሙያዎች የሚወሰን ሲሆን የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም የቅ/ጽ/ቤቱ አመራር ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡
- በአፈጻጸም ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች ሲኖሩ እንደ አስፈላጊነቱ በስጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት በኩል ማኑዋሉ ማሻሻያ ይደረግታል፡፡

# የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

# የታክስ ህግ ተገዥነት ሥጋት ስራ አመራር ዳይሬክቶሬት

---

የካርጐ ስካኒንግ ስጋት ሥራ አመራር

በማኑዋል የሚጣሉ የስጋት ደረጃዎች አሠራር ሥርዓት ማንዋል

ሐምሌ 2007 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 1 |
| 2. ትርጉም | 2 |
| 3. የማንዋሉ ዓላማ | 2 |
| 4. አስፈላጊነት | 2 |
| 5. የተፈጻሚነት ወሰን | 3 |
| 6. የተግባር መግለጫ | 3 |
| 6.1 በጉምሩክ መግቢያ በሮች | 3 |
| 6.2 በስካኒንግ ማሽን የሚፈተሹ ዕቃዎች | 3 |
| 6.3 በስካኒንግ ማሽን የማይፈተሹ ዕቃዎች | 4 |
| 6.4 ስዕላዊ መግለጫ | 4 |
| 6.5 የሚከናወንበት ጊዜ | 4 |
| 6.6 የሚወስደው ጊዜ | 4 |
| 6.7 ፈፃሚ | 4 |
| 7. በማኑዋል የስጋት ደረጃዎችን ለመወሰን የሚያስችሉ አመላካቾች | |
| 7.1 በከፍተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ | 5 |
| 7.2 በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ | 6 |
| 8. በመድረሻ ጣቢያዎች | |
| 8.1 የተግባር መግለጫ | 6 |
| 8.2 በስካኒንግ ማሽን የሚፈተሹ ዕቃዎች | 7 |
| 8.3 በስካኒንግ ማሽን የማይፈተሹ ዕቃዎች | 7 |
| 8.4 ስዕላዊ መግለጫ:- በጉምሩክ መድረሻ ጣቢያዎች | 8 |
| 8.5 የሚከናወንበት ጊዜ | 9 |
| 8.6 የሚወስደው ጊዜ | 9 |
| 8.7 ፈፃሚ | 9 |
| 9. ተጨማሪ የስጋት አመላካቾች | 9 |

# ምዕራፍ አንድ

## 1.መግቢያ

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ዘመናዊ የጉምሩክ አስተዳደርን ለመገንባት ዘርፈ ብዙ ጥረቶችን እያደረገ ይገኛል፡፡ ከዚህም አንዱና ዋነኛው የጉምሩክ አሠራርን ሙሉ በሙሉ የስጋት ሥራ አመራርን መሠረት ባደረገ መልኩ እንዲሆን እና የተቀላጠፈ አገልግሎትና የተመጣጠነ ቁጥጥር እንዲኖር ማስቻል ነው፡፡ የስጋት ሥራ አመራር አለም አቀፋዊ ይዘት ያለው የአሠራር ሥርዓት ሲሆን ለህጋዊ ነጋዴዎች የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት የሚያስችልና ለህጉ ተገዢ ባልሆኑት ላይ ተገቢውን ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ዘዴ ነው፡፡ ይህም መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች በመሰብሰብና በመተንተን ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ፈጣን አገልግሎት አሰጣጥን ከውጤታማ ቁጥጥር ጋር አጣጥሞ ለመተግበር የሚያስችል ስልት ነው፡፡

ዚህ ጋር በተያያዘ የኢ/ገ/ጉ/ባ ገቢን በብቃት ለመሰብሰብ፣ ኮንትሮባንድን ለመከላከል እና የህብረተሰቡን ደህንነት መጠበቅ በከፍተኛ ወጪ ዘመናዊ የዕቃ መፈተሻ መሣሪያ (cargo scanning machine) ቴክኖሎጂ እየተጠቀመ ይገኛል፡፡ ቴክኖሎጂው ውጤታማ የሆነ ቁጥጥር ከማምጣት ጐን ለጐን ለንግዱ ማህበረሰብ የተቀላጠፈ አገልግሎት በመስጠት ዕቃዎች በቁጥጥር ምክንያት በጉምሩክ ጣቢያዎች የሚቆዩበትን ጊዜ ለመቀነስ ታስቦ እየተተገበረ ይገኛል፡፡ እስካሁን ባለው ሂደት እንደ አጠቃላይ ብዙ መልካም ተግባራት ተከናውነዋል ነገር ግን አገልግሎቱ የስጋት ሥራ አመራርን መሠረት ባደረገ መልኩ እየተሰጠ ባለመሆኑ የተፈለገውን ውጤት እያስገኘ አይደለም፡፡ የአገልግሎት አሠጣጡን የተቀላጠፈ ለማድረግ ይቻል ዘንድ ስጋት ሥራ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ በስጋት ሥራ አመራር ያልተደገፈ የካርጐ ስካኒንግ አገልግሎት ንግድን የማሳለጥን ተግባር ከማስተጓጐሉ ባለፈ ቁጥጥር ሊደረግባቸው የሚገቡ ኮንቴነሮችን ለይቶ ትኩረት ማድረግ ሲገባው በሁሉም ላይ ቁጥጥር በማድረግ አላስፈላጊ የሆነ መስተጓጉል ይፈጥራል፡፡

የስጋት ሥራ አመራርን በካርጐ ስካኒንግ ማሽን ላይ ተግባራዊ ማድረጉ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ሲኖሩት በተለይም የዕቃ ወጣጥን ከማቀላጠፍ አንፃር፣ በተሻለ መልኩ የጉምሩክ ጥፋቶችን ከመለየት አንፃር እና ሀብትን በአግባቡ ከመጠቀም ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ በተጨማሪም የተሻለ ቁጥጥር በማድረግና የሀገር ደህንነትን ለመጠበቅ ያስችላል፡፡ በመሆኑም በሲስተም የታገዘ የካርጐ ስካኒንግ ስጋት ሥራ አመራር ሥርዓት እስኪተገበር ድረስ በማኑዋል የአሰራር ስርዓቱን መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖዋል፡፡

ስለዚህ የትራንዚት አሰራር ስርዓት የዕቃ ቁጥጥር በዘመናዊ ቴክኖሎጂ (cargo tracking and electronics seal) እና በተጠናከረ ተንቀሳቃሽ ኢንተለጀንስ ዩኒት ቁጥጥር እንደ ሚደረግበት ታሳቢ ተደርጎ የተቀረጸ ነው፡፡ ይህ ማለት ተፈትሸው ልዩነት የተገኘባቸውም ሆነ የማየፈተሹ ጭነቶች ባሉበት ሁኔታ መድረሻ ጣቢያ መድረሳቸውን ክትትል እንደሚደረግበት ታሳቢ ያደረገ ነው ማለት ነው፡፡

## 2.ትርጉም

### 2.1. የስጋት ሥራ አመራር

የስጋት ስራ አመራር ማለት ወደ ጉምሩክ ክልል በሚገቡ፣ በሚወጡና በሚተላለፉ እቃዎች ላይ አገልግሎት አሰጣጡንና የቁጥጥር ሥርዓቱን ሚዛናዊ ባደረገ ሁኔታ በሚቀመጡ መስፈርቶች መሠረት የተለያየ የስጋት ደረጃ በማውጣት የሚከናወን የአሰራር ሥርዓት ነው፡፡

### 2.2. የጉምሩክ ትራንዚት

የጉምሩክ ትራንዚት ማለት ዕቃዎች በጉምሩክ ቁጥጥር ስር ሆኖ ከአንድ የጉምሩክ ጣቢያ(የተፈቀደ ቦታ) ወደ ሌላ የጉምሩክ ጣቢያ (የተፈቀደ ቦታ) ወይም ከመግቢያ በር ወደ መዉጫ በር ወይም የጉምሩክ ጣቢያ በተፈቀደ መስመር የሚጓጓዝበት ሥርዓት ነዉ፡፡

### 2.3. ካርጐ ስካኒንግ ማሽን

ˋለት ወደ ሀገር የሚገቡ ወይም ከሀገር የሚወጡ ተሽከርካሪዎች የያዟቸው ጭነቶች ወይም ከአገር የሚወጡ እና ˋደ ሀገር የሚገቡ ጓዞች የሚፈተሹበት የዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ነዉ፡፡

## 3.የማንዋሉ ዓላማ

የዚህ ማንዋል ዓላማ የካርጎ ስካኒንግ የፍተሻ ሥርዓት በስጋት ሥራ አመራር ሥርዓት መሰረት እንዲተገበር በማስቻል የስጋት ስራ አመራር ቡድኖች እና ፈጻሚዎች ሙሉ በሙሉ በሲስተም ስጋት ደረጃ እስከሚጣል ድረስ እና በተለያዩ ምክንያቶች በሲስተም የሚጣላ የስጋት ደረጃ ሲቋረጥ /አሲኩዳ ሲስተም ሲቋረጥ/ የሚያከናውኑትን ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ በማስቀመጥ ተጠያቂነትን የሚያሰፍን አሠራር መዘርጋት ነው፡፡

## 4. አስፈላጊነት

የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠትና የቁጥጥር ሂደቱ በወጥነት ተግባራዊ ለማድረግ ማለትም ያልተፈቀዱ፣ገደብ እና ክልከላ የተደረገባቸው፣ ህገወጥ ጭነቶችን እንዲሁም የኮንትሮባንድ ጭነቶችን ለመቆጣጠር ከማስቻሉም በላይ በአንዳንድ ሂደቶች ሊታጡ የሚችሉ ገቢዎችን በብቃት ለመሰብሰብ፣ በሀገር እና በሕብረተሰቡ ደህንነት ላይ ስጋት የሚፈጥሩትን ለመቆጣጠር ማስቻሉ ሲሆን ሲስተም ሙሉ በሙሉ የስጋት ደረጃን እስከሚጥል እና የሲስተም መቆራረጥን በማኑዋል መደገፍ አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

## 5. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ ማኑዋል በዩኒ ሞዳል እና በመልቲ ሞዳል ተጋጉዘው በሚገቡ የገቢ እና ተሳላፊ ዕቃዎች እንዲሁም በመድረሻ ጣቢያዎች በዕቃ ፍተሻ ላይ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 6. የተግባር መገለጫ

### 6.1 በጉምሩክ መግቢያ በሮች

#### 6.1.1 ቅድመ ሁኔታዎች

- በሲስተም/በተለያዩ መንገዶች ቀድሞ የደረሰ መረጃ/ማኒፌስት
- ቀድሞ በደረሰ መረጃ መሰረት የተዘጋጀ የስጋት ደረጃ
- መረጃ ቀድሞ ባልደረሰበት ሁኔታ የተለየ የስጋት አመላካቾችና የስጋት መረጃ
- የጉምሩክ የስጋት ሥራ አመራር አሰራርንና የጉምሩክ ሥርዓትን አፈጻጸም መሰረታዊ ክህሎት

#### 6.1.2 የአፈፃፀም ቅደም ተከተል፤

-የስጋት ስራ አመራር ባለሙያ ከትራንዚት ቁጥጥር ኦፊሰር ሰነድ ይቀበላል፤

-የስጋት ትንተና ያከናውናል፤

-የስጋት ደረጃ ያወጣል፤

-በስጋት ደረጃቸው መሰረት ውሳኔውን ለመስተንግዶ ያስተላልፋል፤

-የመስተንግዶ ውጤቱን ይከታተላል፡፡

### 6.2 በስካኒንግ ማሽን የሚፈተሹ ዕቃዎች


ሀ) ሰነዱ በዚህ የአሰራር ማኑዋል መሰረት ከፍተኛ ስጋት ከሆነ የስጋት ደረጃውን በማረጋገጥ ወደ ትራንዚት ቁጥጥር ይልካል፡፡ በማኑዋል ከፍተኛ የስጋት ደረጃ የተጣለባቸው ጭነቶች መረጃ በሲስተም (TPRDP) ወይም በexcel በመመዝገብ ወደ ትራንዚት ቁጥጥር ይተላለፋል፡፡

ለ) ሰነዱ በዚህ የአሰራር ማኑዋል መሰረት ዝቅተኛ ስጋት ከሆነ የስጋት ደረጃውን በማረጋገጥ ወደ ትራንዚት ቁጥጥር ይልካል መረጃዉንም በሲስተም (TPRDP) ወይም በexcel ይመዘግባል፡፡

## 6.3 በስካኒንግ ማሽን የማይፈተሹ ዕቃዎች

በስካኒንግ ማሽን የማይፈተሹ ዕቃዎች በየዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 58/2003 አንቀጽ 5 መሰረት ወይም በሌሎች የመስሪያቤቱ ያሰራር ድንጋጌዎች፣መመሪያዎች፣ማኑዋሎች የማይፈተሹ ተብለው የተገለጹ ዕቃዎች ናቸው።

## 6.4 ስዕላዊ መግለጫ፡- በጉምሩክ መግቢያ በሮች




## 6.5. የሚከናወንበት ጊዜ

- ከትራንዚት ቁጥጥር ሰነድ ሲተላለፍ በማንኛውም ሰዓት

## 6.6.የሚወስደው ጊዜ

- ሶስት ደቂቃ

## 6.7.ፈፃሚ

የስጋት ሥራ አመራር ቡድኑ እና ኦፊሰር

7. በማኑዋል የስጋት ደረጃዎችን ለመወሰን የሚያስችሉ አመላካቾች

7.1. በከፍተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ

ሀ. ከኢተለጀንስና ከተለያዩ አካላት ጥቆማ የሚቀርብባቸው

ለ. የተረጋጋ የፖለቲካ ስርዓት ከሌላቸው ሀገራት የተመረቱ ወይም የተጫኑ ከሆነ (ለምሳሌ ሶማሊያ፣ ሲሪያ፣ አፍጋኒስታን፣ ኮንጎ፣ ሱዳን፣ የመን፣ ሊቢያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ኢራክ፣ እና የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሮክቶሬት በሚልካቸው መረጃዎች መሰረት)

ሐ. በአደንዛዠ ዕጽ ዝውውር ከታወቁ ሀገራት የተጫኑ ከሆነ (ለምሳሌ አፍጋኒስታን፣ ፓኪስታን፣ ኮሎምቢያ፣ ሜክሲኮ፣ ታይላንድ፣ ናይጀሪያ እና የታክስ ህግ ተገዥነት ስጋት ስራ አመራር ዳይሮክቶሬት በሚልካቸው መረጃዎች መሰረት)

መ. በመንገድ ወረቀቱ ላይ ጨረር አመንጪ ዕቃዎች የተገለጹ ከሆኑ

ሠ. በመንገድ ወረቀቱ (T1) ላይ ሪማርክ የተፃፈ ከሆነ

ረ. ኤክሳይዝ ታክስ የተጣለባቸው ዕቃዎች ሲመጡ በግልጽ በማየት መለየት የማይቻሉ ከሆነ (ከታች በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የተመደቡትን ሳይጨምር)፤

ሸ. ዕቃዎች ካላቸው ባህሪ አንጻር የማጭበርበር ድርጊት የሚፈጸምባቸው በየወሩ በፍተሻ እና ሰነድ ምርምራ ሪፖርት የቀረበባቸው፤ /ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል ከሚገኙ መረጃዎች/

ቀ. ሶስት እና ከዚያ በላይ የከባድ ጥፋት ሪከርድ ባለባቸው የጉምሩክ ስነ-ስርዓት አስፈጻሚዎች የሚስተናገዱ ሰነዶች፤ /ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል ከሚገኙ መረጃዎች/

በ. የልዩ የጉምሩክ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እና የታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች (AEO) ዕቃዎች ከሌሎች ጭነቶች ጋር ተቀላቅለው ሲመጡ፤

ተ. በሚያዙ የጥፋት መረጃ መሰረት በተደጋጋሚ የአገላለጽና የትርፍ ልዩነት የሚገኝባቸው ድርጅቶች ሲያስመጡ፤ ወይም በተደጋጋሚ የሰነድ ምርመራ፣ የፍተሻ እና የድህረ ዕቃ አወጣጥ ግኝት የሚገኝባቸው አስመጭዎች የሚያስመጧቸው ዕቃዎች፤ (ከTPRDP ወይም ከሌሎች በሲስተም ወይም በማኑዋል በተያዙ መረጃዎች መሰረት)

ቸ. ከጭነቱ ጋር የማይሄድ የተጋነነ ትራንስፖርት ወጪ፤ (ከዕቃው ጋር ተመጣጣኝ ያልሆኑ የትራንስፖርት ክፍያዎች መኖሩ ሲረጋገጥ)፤

ነ. ተሽከርካሪው ከሚጠበቅበት ጊዜ በላይ ዘግይቶ ሲደርስና አሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ፤

ኘ. መኪናው በተነሳበት ሁኔታ የደረሰ ካልሆነና አጠራጣሪ ሁኔታ ሲኖር (ሲሉ የተበጠሰ ከሆነ)፤

አ. የንግድ እቃዎች በብትን ጭነቶች ሲመጡ፤

ከ. የሲል ቁጥር ልዩነት ሲኖር፤

ወ. በክፍልፋይ የሚጓጓዙ ጭነቶች፤

.2. በዝቅተኛ የስጋት ደረጃ የሚመደቡ

ሀ. ትላልቅ ወይም ግዙፍ  እቃዎች ሆነው በአይን በማየት ብቻ የሚለዩ (የፋብሪካና የፕሮጀክት ማሽነሪዎች እና ዕቃዎች)፣

ለ. በመንግስት እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚገቡ ዕቃዎች፣

ሐ. በትምህርት ተቋማት የሚገቡ የትምህርት መገልገያ መሳርያዎች፤

መ. በታማኝ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች (AEO) የሚገቡ ዕቃዎች፣

ሠ. በቬና ኮንቬንሽን እና በሌሎች ስምምነቶች መሰረት ያለመፈተሸ መብት የተሰጣቸው ሲያስመጡ፣

ረ. በጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጣቃሚ የሆኑ አምራች ድርጅቶች የሚገቡ፣

ሸ. ክፌት ጭነቶች ሲመጡ በማየት ብቻ ማለፍ የሚችሉ ከሆነ፤

8. በመድረሻ ጣብያዎች

8.1 የተግባር መገለጫ

8.1.1 ቅድመ ሁኔታዎች

- የስጋት አመላካቾች እና የስጋት መረጃዎች
- የጉምሩክ የስጋት ሥራ አመራር አሰራርንና የጉምሩክ ስነ ሥርዓት መሰረታዊ ክህሎት

8.1.2 የአፈፃፀም ቅደም ተከተል፤

-የስጋት ስራ አመራር ባለሙያ ከፈዝቤት ሰነድ ይቀበላል፤

-የስጋት ትንተና ያከናውናል፤

-የስጋት ደረጃ ያወጣል ፤

-በስጋት ደረጃቸው መሰረት ውሳኔውን ለመስተንግዶ ያስተላልፋል፤

-የመስተንግዶ ውጤቱን ይከታተላል፡፡

8.2 በስካኒንግ ማሽን የሚፈተሹ ዕቃዎች

ሀ) ሰነዱ ቀይ ሲሆንና በቅ/ጽ/ቤቶች ስጋት ሥራ አመራር ማኑዋል መሠረት ከሌሎች የስጋት ደረጃዎች ወደ ቀይ የስጋት ደረጃ ሲቀየር እና በአንድ ሰነድ በዕቃ አይነት (ከሚሰጡት አገልግሎት ወይም በታሪፍ አመዳደብ) ከሶስት አይነት ዕቃ ወይም የሚመደቡበት የታሪፍ አንቀጽ ከሦስት የማይበልጥ ከሆነ ወደ ገቢ ዕቃ ቡድን ይላካል፡፡

ለ) ሰነዱ ቀይ ሲሆንና በቀላሉ ተሰባሪና ለብልሽት የሚጋለጡ ዕቃዎች


ሐ) የተመረጡ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾች እና የጉምሩክ ልዩ አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚያስመጡት ዕቃ አልፎ አልፎ (Randomly) በቀይ የስጋት ደረጃ ሲመረጥ

መ) የስጋት ደረጃቸው ዝቅተኛ(አረንጓዴ) እና መካከለኛ (ቢጫ) ሆነው መረጃን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ኣጠራጣሪ የሆኑ ዕቃዎች

ን.3 በስካኒንግ ማሽን የማይፈተሹ ዕቃዎች

በስካኒንግ ማሽን የማይፈተሹ ዕቃዎች በየዕቃ ፍተሻ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 58/2003 አንቀጽ 5 መሰረት ወይም በሌሎች የመስሪያቤቱ የአሰራር ድንጋጌዎች፣መመሪያዎች፣ማኑዋሎች የማይፈተሹ ተብለው የተገለጹ እና በመግቢያ በር ተፈትሸው የምስል መረጃቸው ለመድረሻ ጣቢያ የደረሱ ዕቃዎች ናቸው፡፡

8.4. ስዕላዊ መግለጫ፡- በጉምሩክ መድረሻ ጣብያዎች



8.5.የሚከናወንበት ጊዜ

- ከፌዝቤት ሰነድ ሲተላለፍ በማንኛውም ሰዓት

8.6.የሚወስደው ጊዜ

- ሶስት ደቂቃ

8.7.ፈፃሚ

የስጋት ሥራ አመራር ቡድኑ እና ኦፊሰር

## 9. ተጨማሪ የስጋት አመላካቾች

ከዚህ በታች የተገለጹት የስጋት አመላካቾች (Risk Indicators) እንደ አስፈላጊነቱ በመግቢያ በሮች እና በመድረሻ ጋች የስጋት ደረጃን በማኑዋል ከፍ ለማድረግ ይጠቅማሉ፡፡

1. የመጀመሪያ አስመጪ/ላኪ፤
2. ጥቅል የእቃዎች አገላለጽ በዲክላሬሽኖች ወይ በመንገድ ወረቀት ላይ መኖሩ፤
3. በጋራ /ከአንድ በላይ በሆኑ አስመጪዎች / የተጫኑ ጭነቶች፤
4. የተጫነው እቃ ከአስመጪው ቢዝነስ ጋር ተመሳሳይ አለመሆን፤
5. ከጭነቱ ጋር የማይሄድ የተጋነነ ትራንስፖርት ወጪ፤ (ከእቃው ጋር ተመጣጣኝ ያልሆኑ የትራንስፖርት ክፍያዎች)፤
6. ዕቃ ገቢ/ወጪ ለማድረግ የሚጠቀሙበትን ቅርንጫፍ ጽ/ቤት በተደጋጋሚ የሚቀያይሩ፤
7. ዶክሜንት በአሲኩዳ አሰስ አድርገው ትራንዚት ከተፈቀደ በኋላ ከተፈቀደው ትራንዚት ጊዜ በላይ አዘግይተው እቃዎችን የሚያስገቡ/ (excessive delay between document processing and imports)፤
8. እቃው እና የተጫነበት ኮንቴይነር በዶክሜንት ከተገለጸው መጠን ከሚገባው በላይ /ባልተለመደ ሁኔታ / በጣም መክበድ/ /መቅለል/፤
9. ኢምፖርት የተደረበት ቀንና ኤክስፖርት ከሚደረግበት ሀገር የተመዘገበው ጊዜ ከሚገባው በላይ መዘግየት፤
10. የእቃዎች ምርት መለያ ቁጥር የተደለዘ ፤የተሰረዘ እንዲሁም የተቀየረ መሆን
11. የእቃዎች ኦሪጅን ከእቃው ባህሪ ጋር ያልተለመደ መሆን፤
12. ከፍተኛ የኢንሹራንስ ክፍያዎች፤
13. ዲክላሬሽን ላይ የተገለጸው የእቃው መዳረሻ ቦታ በቢልኦፍ ሎዲንግ ከተገለጸው ቦታ ጋር የተለያየ መሆን፤
14. በተደጋጋሚ ሪከርድ ያለበት ትራንስፖርተር የሚመጡ እቃዎች፤

ይህ ማኑዋል ግብአቶች እየተሰበሰቡ እንዳስፈላጊነቱ በየአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚሻሻል ይሆናል፡፡